# የግዕዝ ፊደል የዩናይትድ ስቴትስ የባለቤትነት መብት አገኘ።

*መጋቢት ፳፯ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም.*



ዋና መሥሪያ ቤቱ ብራይተን ኮሎራዶ የሆነው የኢትዮጵያ ኮምፕዩተሮችና ሶፍትዌር ቍጥሩ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ኃምሳ ሰባት የሆነ የዩናይትድ እስቴትስ የባለቤትነት መታወቂያ (ፓተንት) መጋቢት ፳፱ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም. ማግኘቱን አስታወቀ። (http://patents.com/us-9000957.html) ፓተንቱ የተሰጠው ለፈጠራውና የኩባንያው ባለቤት ለዶ/ር አበራ ሞላ ሲሆን ኩባንያው የእርሳቸውንና የባለቤታቸው የሠናይት ከተማ ነው።

“አብሻ” ሥርዓት በመባል በታወቀው አዲስ ዘዴ መጀመሪያ መርገጫ ላይ ያሉት ቀለሞች የሚከተቡት እያንዳንዳቸው በአንድ መርገጫ ሲሆን ሌሎቹ በሁለት መርገጫዎች ብቻ ነው። ይህ ኮምፕዩተሮች፣ የእጅ ስልኮችና ተመሳሳይ መሣሪያዎች ውስጥ የእንግሊዝኛ ፊደላት ከሚከ ተቡበት አንዳንድ ዘዴዎች ጋር የተቀራረበ ነው። በተጨማሪም ቍጥሩ 20090179778 (http://www.google.com/patents/US20090179778) የሆነውን የፈጠራውን ገለጻ የአሜሪካ መንግሥት ከአተመበት ሐምሌ ፱ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም. ወዲህ የዶክተሩን ጽሑፍ የጠቀሱ ስድስት አዳዲስ የአሜሪካ ፓተንቶች ለሌሎች ተሰጥተዋል።

የእዚሁ (Ethiopian Character Entry) የባለቤትነት መታወቂያ ቍጥሩ ET/P/2009/111 የሆነ ከኢትዮጵያ ለዶክተር አበራ ሞላ እንደሚሰጥ ጥቅምት ፳፱ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም. (September 9, 2015) ለጠበቃዎቻቸው ተገልጿል።

ግዕዝ ከዓለም ጥንታዊ ፊደላት አንዱ ሲሆን ኢትዮጵያውያን ከሺ ዘመናት በላይ ተጠቅመውበታል። የማተሚያ መሣሪያ ወደ ኢትዮጵያ በ፲፱፻፬ ዓ.ም. ገደማ እስከገባበት ድረስ ፊደሉ የሚከተበው በእጅ ጽሑፍ ብቻ ነበር። በኮምፕዩተር ቴክኖሎጂ መፈጠር የተነሳ ዶ/ር አበራ የግዕዝን ፊደል ለመጀመሪያ ጊዜ ኮምፕዩተራይዝ ሲያደርጉ እያንዳንዱ ቀለም በሁለት መርገጫዎች እንዲከተብ በ፲፱፻፸ ዓ.ም. አቅርበው በግዕዝ ፊደል በኮምፕዩተር መጠቀም በግዙፍ ተስፋፍቷል። ከእዚያም ወዲህ ብዛቱ ወደ ፭፻ የሚጠጋው የግዕዝ ቀለም እያንዳንዱ የእራሱ ቍጥር እንዲኖረው ለተቋቋመ ዩኒኮድ (Unicode) የሚባል ድርጅት ቀርቦ በዓለም ደረጃ ዕውቅና አግኝቷል። ትክክለኛዎቹና ሁሉም የግዕዝ ቀለሞች የዩኒኮድ መደብ ውስጥ እንዲገቡ ዶክተሩ ትልቅ አስተዋጽዖም አድርገዋል።
http://www.ethiopianstories.com/component/content/article/55-science-a-technology/125-dr-abera-molla

አስቸጋሪ ሆኖ የቆየው ግን በኮምፕዩተር መርገጫዎች ቍጥር ማነስ የተነሳ ቀለሞቹን ከሁለት መርገጫዎች በአነሰ በኮምፕዩተር የመከተብ ከባድነት ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ እያንዳንዱ ቀለም በሁለት መርገጫዎች የሚከተቡበትን እናሻሽላለን ብለው ሌሎች ከአቀረቧቸው ዘዴዎች መካከል በማውስ ቀስት መልቀም፣ አንዳንዶቹን ቀለሞች ከሦስት እስከ ስምንት መርገጫዎችን በመጠቀም ለመከተብ መዘጋጀት፣ ባዶ ስፍራ ቃል መካከል መጨመር፣ የግዕዝን ፊደል በላቲን ፊደል አጻጻፍ ለመከተብ እስፔሊንግ መማር፣ የማይጽፏቸው ቃላት መኖርና ፊደል መቀነስ ይገኙበታል። አዲሱ ፈጠራ ኢትዮጵያውያንን ከእነዚህ ችግሮችና በአድልዎ ከመከፋፈልና መዳከምም አላቋል። በፓተንት ማመልከቻው እንደተጠቀሰው የፈጠራው አስፈላጊነት ግዕዝን በቀላሉና በቀለጠፈ ዘዴ መከተብ የሚያስችል ዘዴ ስለአልነበረ ነው። የዓማርኛ ቀለሞችን በብዙ መርገጫዎች መከተብ የተጀመረው እንግሊዝኛ ለቃላቱ የሚጠቀምበትን የእስፔሊንግ ዘዴ ለዓማርኛ ፊደል መከተቢያ እንዲሆን አንዳንዶቹ ስለፈለጉና ስለአልተሳካም ነው። እንግሊዝኛ ቃላትን እንጂ ቀለሞቹን በእስፔሊንግ አይከተብም። ግዕዝ ድምጻዊ ፊደል ስለሆነና እንደ

እንግሊዝኛው ዓይነት የእስፔሊንግ ችግር ስለሌለው ተገልጋዩ ኣሠራሩን በግሉ ተምሮ መጠቀም ይችላል። ፈጠራው ቀላልና ትክክለኛ ስለሆነ መረዳት ከኣለማስቸገሩም ሌላ ዓማርኛ በብዛት የሚጠቀምባቸው ሳድሳን ቀለማት የሚከተቡት በኣንድ መርገጫ ነው። በእዚህ ኣዲስ የፈጠራ ግኝት የተነሳ ኣንድን ኃሳብ በዓማርኛ ወይም ሌሎች የግዕዝ ፊደል ተጠቃሚ ቋንቋዎች በቀላሉ ማቅረብ ተችሏል። ምክንያቱም የኣብሻ ሥርዓት ኮምፒዩተር ለእንግሊዝኛ ቀለሞች ከሰጠው ኃይል የበለጠና የረቀቀ በመሆኑ ግዕዝ ኣዲስ ኃይል ስለኣገኘ ነው። የመርገጫዎቹ ቁልፎች ኣመዳደብ የተመረኰዘው የእንግሊዝኛው ላይ ስለሆነ የግዕዝ ተጠቃሚው ኣከታተብ በቀላሉ በመማር ከኣንድ ገበታ መክተብ ይችላል። ግዕዙን በኣንድና ሁለት መርገጫዎች በግዕዝ ፊደል የመክተብ ኣስፈላጊነት የግዕዝና ላቲን ኣከታተቦች ግንኙነት ስለሌላቸው ነው። ስለዚህ ማንኛውንም የግዕዝ ቀለም በሦስት መርገጫዎች መክተብ ጊዜና ጉልበት ማባከን ነው። የተሳሳቱ ኣከታተቦችና ቀለሞች መጠቀም ተለምደው መቸገርና ማስቸገርንም ያስቀራል። የግዕዝና የላቲን ፊደሎችን ቀላቅሎ መሥራትና መፈለግ ይቻላል። የእንግሊዝኛው የጽሕፈት መሣሪያና ኮምፒዩተር ብዙ ፓተንቶች ሲኖሩት ይህ ፓተንት ለግዕዝ ፊደል የመጀመሪያው ነው።

በግዕዝ ፊደል በእየራሳቸውና በሚጋሯቸው ቀለሞች ከሚከተቡ ቋንቋዎች መካከል ቢለን፣ ቤንች፣ ሙርሲ፣ ምኢን፣ ሱሪ፣ ቅማንት፣ ቋራ፣ ትግረ፣ ትግርኛ፣ ዲዚ፣ ዳውሮ፣ ጉሙዝ፣ ጉራጌ፣ ጋሞ ጎፋ፣ ግዕዝ፣ ካይላ፣ ኩንፈል፣ ኣውንጂ፣ ኦሮሚፋ፣ ዓማርኛ እና ጫምታንግ ይገኙበታል። ዶ/ር ኣበራ ለግዕዝ ፊደል ፈር-ቀዳጅ ተመራማሪ ብቻ ሳይሆኑ ለግዕዝ ኣስፈላጊ ናቸው ብለው ከሠሯቸው ኣዳዲስ ቀለሞች መካከል የግዕዝ ኣልቦ፣ ብር፣ ሣንቲም፣ መብት፣ ንግድ፣ የተመዝግቧል፣ ማጥበቂያና ሌሎች ምልክቶች ኣሉ። የኮምፒዩተሩን የላቲን ምልክቶች ለግዕዝ ጥቅም ኣውለውና ከተዘረዘሩት ቋንቋዎች ቀለሞች ጥቅም ኣልፈው መርገጫዎቹ ተርፈዋል። የዶክተሩ የግዕዝ ፊደል ተመጣጣኝ የሆነ የእራሱ የእንግሊዝኛ ፊደልን ያካትታል።

ፓተንት እየተጠበቀ ነው በሚል ማስጠንቀቂያ ኩባንያው ከግዕዝኤዲት ዶት ኮም ([http://www.geezedit.com)](http://www.geezedit.com) ድረገጽ ግዕዝኤዲት ክፍል ሁለትን ለጥቂት ዓመታት ለገበያ ሲያቀርብ ቆይቷል። ኢንተርኔት ላይ ነፃ የዓማርኛ መክተቢያ ከ፳፻፬ ዓ.ም. ጀምሮ ለዊንዶውስና ማክ ኮምፕዩተሮች ኣቅርቧል። ([http://freetyping.geezedit.com](http://freetyping.geezedit.com)) በ፳፻፮ ዓ.ም. ኣፕል የኣይኦኤስ 8 ሥርዓቱን በመክፈት ሌሎች መክተቢያዎቻቸውንና ፊደሎቻቸውን እንዲያስገቡ ስለፈቀደ ኩባንያው የግዕዝኤዲትን (GeezEdit App) ቁስ (ኣፕ) ለኣይፎን 6 እና ኣይፓድ ኣቅርቧል። የኣይፎን 4ኤስ እና 5 ሥርዓት ወደ ኣይኦኤስ 8 ከተሻሻለ በግዕዝኤዲት ቁስ መሥራት ይቻላል። ቁሱ የዓማርኛ ቀለሞችን በኣንድና ሁለት መርገጫዎች እንደሚከትበው ዓይነት የሌሎች ቋንቋዎች መክተቢያዎችም ወደፊት ይከፈታሉ። ነፃው ግዕዝኤዲት፣ ለዊንዶውስ የሚሸጠውና ግዕዝኤዲት ቁስ ሦስቱም የሚከተቡት በፓተንትና እየተጠበቁ በኣሉ ፓተንቶች በተጠበቁ የኣከታተብ ዘዴዎች ነው። ቁሱ ከሚያስከትብባቸው ፕሮግራሞች መካከል ቴክስት፣ ኢ.ሜይል፣ ሜሴጅስ፣ ፌስቡክ፣ ትዊተር፣ ኖትስ፣ ማይክሮሶፍት ወርድ፣ ኦፌስ ስዊት፣ ፔጅስ፣ ጉግል፣ ያሁ ፣ ቢንግ፣ ዊኪፒዲያና ኋትስኣፕ ይገኙበታል። የዓማርኛው ቁስ ኣጠቃቀሙን ከእንግሊዝኛው ሥርዓት ጋር ስለሚጋራ በሁለቱም ፊደላት መሥራት ያስችላል። የእስማርት (ረቂቅ) ስልኩ በዓማርኛ ቋንቋ እንዲሠራ መምረጥ ይቻላል። ዓማርኛ ኣብዛኛው ሕዝብ የሚጠቀምበት የኢትዮጵያ ፊደል ሲሆን ፈጠራው የኣናሳ ቋንቋዎች ቀለሞች በብዙ መርገጫዎች እንዲከተቡ የሚደረገውን ግፊትና ፊደል ስለበዛ መጻፍ እንዳያስቸግሩ ይቀነሱ የሚባለውን ኣስተሳሰብ ሊያስቀር ይችላል። የግዕዝኤዲት ቁስ እዚህ ይገኛል፦ [https://itunes.apple.com/us/app/geezedit/id935624754?mt=8](https://itunes.apple.com/us/app/geezedit/id935624754?mt=8)

ግዕዝ ድምጻዊ ፊደል ስለሆነ ኣንድን ኃሳብ በጥቂት ቀለማትና ስፍራ በጥራት የማቅረብ ችሎታ ሲኖረው ፈጠራው ተጨማሪ ኃይል ሰጥቶታል። ለምሳሌ ያህል በፈጠራው ጥቅም የተነሳ በዓማርኛ “ዘ ኲክ ብራውን ፎክስ ጀምፕስ ኦቨር ዘ ሌይዚ ዶግ።” የሚለውን በእንግሊዝኛ “The quick brown fox jumps over the lazy dog.” እንደሚጻፈው ሁለት ገበታዎች ኣያስፈልጉትም። እንዲሁም “ሐመር ኋይት ሃውስ ሦስት ቋንቋ ትዕግሥት ጨካኝ” ምሳሌ 23 የዓማርኛ ቀለሞች በኣብሻ ሥርዓት የሚከተቡት በ32 እስከ 34 መርገጫዎች ሲሆን እንደ ሌሎቹ ከ50 በላይ የዓማርኛ መርገጫዎችን መጠቀም ኣያስፈልግም። በተጨማሪም የዓማርኛውን “ጨ” በኣራትና ኣምስት መርገጫዎች መክተብ

የጉራጌኛ ወይም የጉሙዝ “ጨ”ዎች በእንግሊዝኛ እስፔሊንግ መክተብ እስከ ሰባትና ስምንት መርገጫዎችን መጠቀም ስለሚያስከትል የኣናሳ ቋንቋዎች ተጠቃሚዎች እንዳይቀየሙ ፈጠራው ይራዳል። ምክንያቱም በፈጠራው የተነሳ ማንኛውንም የግዕዝ ቀለም በኣንድና ሁለት መርገጫዎች መክተብ ስለተቻለ ነው።

በላቲን ኣከታተብ ሥርዓት 26ቱ መርገጫዎች የተመደቡት ለእያንዳንዱ ቀለም ሲሆን ለ37ቱ የግዕዝ ቀለሞችም ዶክተሩ ግዕዝን ዲጊታይዝ (Digitize) ሲያደርጉ ለእያንዳንዱ ቁልፍ ተመድቦላቸዋል። ግዕዝ በላቲን 26 መርገጫዎች ካልተጻፈ ብለው ጥቂቶቹ የቁልፍ እጥረት ከፈጠሩ በኋላ ይኸንኑ ችግር የዝቅ (ሺፍት) ገበታ ላይ በመድገም ግዕዝ የማያውቀውን የእስፔሊንግ ችግር መፍጠር የሚፈልጉም ኣሉ። ግዕዝ ኮምፕዩተራይዝ ሲደረግ ፓተንቱ ኣሁንም ስለኣልተሰጠ የተለያዩ መክተቢያዎች ቀርበው ሕዝቡ ሲበሳጭ የነበረውን ኣዲሶቹ ፓተንቶች እንዲያስቀሩ ማስተዋልና መጠንቀቅ ኣስፈላጊዎች ናቸው። የፓተንቶቹ መኖር ኢትዮጵያውያን ኣዳዲስ የግዕዝ ቴክኖሎጅዎችን ፈጥረው እንዲገነቡባቸውና ፓተንቶች እንዲያገኙ የሚረዱ የጥበቡ መጀመሪያ መሠረቶች ናቸው። ይኸን ተረድቶና መከተል የትውልዱ ኃላፊነት ነው።

ዶክተሩ ግዕዝ በኮምፕዩተር እንዲሠራ ሲፈጥሩ ሁለት መርገጫዎችን በመጠቀም መክተብ የሚቻለው ስድስት ቀለሞችን ብቻ ሲሆን ኣዲሱ ፈጠራ ይኸንኑ ወደ 14 ቀለሞች ከፍ ኣድርጎታል። ስለዚህ ቃላት ይመስል የግዕዝ ቀለሞችን በእንግሊዝኛ ፊደል እስፔሊንግ መክተብ ወይም የእንግሊዝኛ ኣክሰንቶች እንደሚከተቡት መንኰቀቅ ኣያስፈልግም። ምክንያቱም የዝቅ መርገጫን መጠቀም ሳያስፈልግ ሁሉንም የግዕዝ ቀለሞች ከኣንድ ሰሌዳ ብቻ መጠቀም ስለተቻለ የምሁራን የፓተንትን ጥቅም ማወቅና ማሳወቅ የእራሳቸውንና የኣገሪቱን መብቶች ለመጠበቅ ስለሚራዳ ነው። ዶክተሩ በምርምራቸው በመራቀቅ ኣዳዲስ ፈጠራዎቻቸውን በማቅረቡ ቀጥለውበታል። http://patents.justia.com/patent/20150212592




የዶክተሩ ሙያ እንስሳት ሕክምና ሲሆን በመስኩም ትላልቅ ኣስተዋጽዖዎች ከማድረግ ሌላ ፓተንቶችም ኣሏቸው። ለተጨማሪ መረጃ ኢ.ሜይሉ Geezedit@aol.com ነው።

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
April 10, 2016